# ጋዜጣዊ መግለጫ

የአሜሪካ ኤምባሲ፤



አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ
*2016/32*

ለተጨማሪ መረጃ ቀጥሎ በተመለከተው ቁጥር ይደውሉ፡-011-130-7033
ድረ-ገጽ፡- http://ethiopia.usembassy.gov

## የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ የሳንባ ነቀርሳን ለመግታት ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ያለውን አጋርነት እንደሚያጠናክር አስታወቀ

*አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ፤ ሰኔ 21 ቀን 2008 ዓ.ም.፡-* የአሜሪካ መንግሥት በዓለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲው በኩል እና ከኢፌዲሪ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፤ እንዲሁም አጋር ከሆኑት ኬ.አን.ቪ.ሲ የሳንባ ነቀርሳ ፋውንዴሽን፣ ሥራ አመራር ለጤና ሳይንስ (MSH)፣ እንዲሁም ከዓለም የጤና ድርጅት(WHO) ጋር በመተባበር፣ በዛሬው ዕለት የሳንባ ነቀርሳን መፈወስ የተሰኘው እንቅስቃሴ ሳንባ ነቀርሳን እንታገለው ወደሚል ምዕራፍ መሸጋገሩን አብስሯል፡፡

ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና ከአማራና ኦሮሚያ ክልል የጤና ቢሮዎች ጋር ተቀናጅቶ በመሥራት፤ የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ( USAID) ሳንባን ነቀርሳን መፈወስ የተሰኘ መርሀ ግብር፤ ሚኒስቴሩ ከሐምሌ 2003 ዓ.ም. ጀምሮ 16 ሚሊዮን የሚሆኑ ህሙማንን በምርመራ መለየት ችሏል፡፡ ይህ እንቅስቃሴ በተጀመረበት ወቅት 1,000 የሚሆኑ የጤና ተቋማትን አገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻል እንደ ግብ የተያዘ ግብ ቢሆንም፤ ሚኒስቴሩ ይህንኑ በማስፋፋት በእነዚህ ክልሎች የሚገኙ 2,200 የጤና ተቋማት በመርሀ ግብሩ እንዲታቀፉ አድርጓል፡፡

ከአጋሮቹ ከአለርት፣ ከፓዝ፣ እንዲሁም ከኬንያ ሳንባ ነቀርሳና የሳንባ በሽታዎችን መከላከያ ማኅበር ጋር በመሆን፤ ሥራ አመራር ለጤና ሳይንስ (MSH) የተሰኘው ድርጅት ሲተገብረው የቆየው ይህ ሳንባ ነቀርሳን መፈወስ የተሰኘው መርሀ ግብር፣ ለሳንባ ነቀርሳ ምርመራ የላቦራቶሪ ትስስርን ከማጠናከሩም በላይ ከ250,000 በላይ የሚሆኑ ህሙማን የሕክምና አገልግሎት እንዲያገኙ አድርጓል፡፡ በተጨማሪም ኤጀንሲው ዘርፈ-ብዙ መድኃኒት ተቋቋሚ ሳንባ ነቀርሳ ላይ ያተኮረ ሞዴል መርሀ ግብር ዘርግቶ የሳንባ ነቀርሳና የኤች አይ ቪ አገልግሎቶች ተቀናጅተው እንዲሰጡ፤ በዞንና በየአካባቢው ሳንባ ነቀርሳን በሚመለከት ከፍ ያለ ሙያዊ ግንዛቤ እንዲዳብር በርካታ ሥራዎችን ሠርቷል፡፡

የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ ዳይሬክተር ዴኒስ ዌለር ባደረጉት ንግግር፡- “እነዚህ ያገኘናቸው ውጤቶች ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱና ከክልል የጤና ቢሮዎች ጋር ጠንካራ ትብብርና አጋርነት ባይኖረን ኖሮ ፈጽሞ የማይታሰቡ ነበሩ፡፡” አክለውም ሥራ አመራር ለጤና ሳይንስ (MSH) ይህንን ከፍተኛ ውጤት ለማስመዝገብ ላደረገው ያላሰለሰ ጥረት ምስጋናቸውን አቅርበዋል፡፡

ኢትዮጵያ አሁንም በዓለማችን ላይ ሳንባ ነቀርሳ በከፍተኛ ሁኔታ ከተንሰራፋባቸው 30 ሀገራት አንዷ ስትሆን፤ በዓመት ወደ 200,000 የሚጠጉ ሰዎችም በዚሁ በሽታ ይጠቃሉ ተብሎ ይገመታል፡፡ ከነዚህም ተመርምረው ሕክምና የሚያገኙት አንድ-ሦስተኛ የሚሆኑቱ ብቻ ናቸው፡፡ በኢትዮጵያ በ2006 ዓ.ም. 1,300 አዲስ የዘርፈ-ብዙ መድኃኒት ተቋቋሚ ሳንባ ነቀርሳ ተጠቂዎች የነበሩ ሲሆን፤ ከነዚህም ሕክምና ማግኘት የቻሉት 45 ከመቶ በታች ናቸው ፡፡ በኢትዮጵያ የሳንባ ነቀርሳ በሽታን መከላከልና ተገቢውን ሕክምና ማቅረብ የአሜሪካ መንግሥት ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው፡፡

ይህ አዲሱ ሳንባ ነቀርሳን እንታገለው የተሰኘ መርሀ ግብር የኢትዮጵያ መንግሥት በመላ ሀገሪቱ ሳንባ ነቀርሳን ሙሉ በሙሉ ለመግታት የሚያደርገውን ጥረት በሚገባ ያግዛል ተብሎ ይታመናል፡፡ ከዚህም አኳያ ሳንባ ነቀርሳን መፈወስ በተሰኘው መርሀ ግብር በኩል የተሠሩ ሥራዎችን በይበልጥ ያጠናክራል፤ያስፋፋል፡፡ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በየክልሉ ለሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎችም ጠንካራ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

የሳንባ ነቀርሳን መታገል የተሰኘው መርሀ ግብር ከሀገሪቱ የጤናው ዘርፍ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ጋር የተቃኘ ከመሆኑም በላይ፤ የሳንባ ነቀርሳ ሕክምና አገልግሎት አቅርቦትን ከማሻሻል፣ህሙማንን ለተሻለ ሕክምና ወደ ሌሎች ተቋማት ከመላክ፣መረጃና ሪፖርት ከመለዋወጥ አኳያ ያልተማከለ የቴክኒክ ድጋፍ እንዲሰጥ በማስቻል ለኢትዮጵያ መንግሥት በሁሉም እርከኖች አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል። የሳንባ ነቀርሳ ሕክምና አገልግሎት አቅርቦት ተደራሽነትን ማረጋገጥ ሌላው ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ነው። ኬ.ኤን.ቪ.ሲ የሳንባ ነቀርሳ ፋውንዴሽን በትግበራው ሂደት ግንባር ቀደሙን ሚና የሚጫወት ሲሆን፤ ሥራ አመራር ለጤና ሳይንስ (MSH) እና የዓለም የጤና ድርጅት የሥራ አመራር ድርሻውን ይይዛሉ።

####

###